# ቁልፍ ቃላት፡- የአጋዥ መሳሪያዎች መግቢያ

TAP

| ቃል | ትርጓሜ | ምስል |
|---|---|---|
| **ከጆሮ በስተጀርባ ያለ የመስሚያ መርጃ** | ከጆሮ በስተጀርባ[A behind-the-ear (BTE)] የመስሚያ መርጃዎች ከጆሮዎ በላይ በመያያዝ በጆሮ ጀርባ ላይ ያርፋል። ቱቦው የመስሚያ መርጃው ከተበጀ earmold ከሚባል በጆሮ ማስተላለፊያ ውስጥ የሚገባ የጆሮ ክፍል ጋር ይገናኛል። |   |
| **ካቴተር** | ከሽንት ፊኛ ሽንትን ለማሳለፍ ጥቅም ላይ የሚውል ስስ ቱቦ ነው። የሽንት ፊኛቸውን በራሳቸው ወይም በፈቃደኝነት ሽንተው ባዶ ለማድረግ በማይችሉ ሰዎች ጥቅም ላይ ይውላል። |  |
| **አቅመ ደካማ** | ደካማ፣ ልፍስፍስ እና አነስተኛ ጉልበት መኖር። ሰዎች እድሜያቸው እየጨመረ እና ጤናቸው እየወረደ ሲመጣ ብዙ ጊዜ ይከሰታል። | |
| **ሽንትን አለመቆጣጠር** | አንድ ግለሰብ የሽንት ፊኛውን ወይም ሰገራውን እንደፈለገ ለመቆጣጠር ሲከብደው ወይም ሳይችል ሲቀር። | |
| **ንግግር አመንጪ አልያም የሚነኩ ሰአቶች** | ጊዜን በመናገር የሚያሳውቅ ሰዓት። |  |
| **ሠራተኞች** | በአገልግሎት ወይም በድርጅት ውስጥ የሚሰሩ ሰዎች። | |
| **ሮሌተር** | ባለአራት ጎማ የመራመጃ ድጋፍ። |  |
| **ስትሮክ** | በአንጎል ውስጥ የደም ፍሰት መዘጋት። ይህ ሊመጣ የሚችለው ከፊል አካል ደካማ ሲሆን ወይም ሽባ ሲሆን እንዲሁም ለመናገር፣ ስሜትን ለመለየት፣ ለማሰብ እና ለመመልከት ችግሮች ሲገጥሙ ነው። | |
| **WHO የቀዳሚ አጋዥ ምርቶች ዝርዝር** | በዓለም የጤና ድርጅት የተነደፉ የነበሩ ቅድሚያ የሚሰጣቸው አጋዥ መሳሪያዎች ዝርዝር። ዝርዝሩ አገራት የራሳቸውን አገራዊ ቅድሚያ የሚሰጧቸው አጋዥ መሳሪያ ዝርዝሮችን ለመለየትና ለመቅረጽ መጠቀም የሚችሉበት ሞዴል ነው። | |

| | | |
|---|---|---|
| **የአንጎል ልምሻ** | እንቅስቃሴ፣ የጡንቻ ክብደት፣ ሚዛን እና አቋም ላይ ተጽዕኖ የሚያደርጉ የጤና እክሎች ስብስብ ነው። የአንጎል ልምሻ ከመወለድ በፊት፣ በመወለድ ጊዜ ወይም ከተወለደ በኋላ በደረሰ ጉዳት የሚመጣ ነው። | |
| **ዳውን ሲንድረም** | አንድ ግለሰብ ሲወለድ ሊኖርበት የሚችል የጤና እክል ነው። ዳውን ሲንድረም አንዳንድ የጤና፣ የእድገት እና የማገናዘብ (የማሰብ) ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል። ከዳውን ሲንድረም ጋር የሚኖሩ ሰዎች የተለየ አካላዊ ገጽታዎች ሊኖሯቸው ይችላል። | |
| **የአከርካሪ ዘንግ ጉዳት** | የአከርካሪ ዘንግ ጉዳት፣ በአብዛኛውን ጊዜ በአደጋ ወይም በህመም ምክንያት ይከሰታሉ። ከአከርካሪ ዘንግ ጉዳት በኋላ፣ መልእክቶች በአካል እና በአንጎል መካከል በአከርካሪ ዘንግ በኩል መጓዝ አይችሉም። አብዛኛውን ጊዜ አንድ ግለሰብ የጉዳት ደረጃ ከደረሰበት ቦታ በታች መንቀሳቀስ እና ስሜት ሊሰማው አይችልም። | |